ኢትዮጵያ (ደረጃ 2)

የኢትዮጵያ መንግሥት ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመግታት ያስችላሉ የተባሉ መሰረታዊ መመዘኛዎችን ሙሉ በሙሉ ማሟላት ባይችልም ከፍተኛ ጥረት ግን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ከቀድሞው የሪፖርት ወቅት ጋር ሲነፃፀር መንግሥት በጠቅላላው የተሻለ ጥረት ማድረጉን እያሳየ በመሆኑ ኢትዮጵያ አሁንም በደረጃ 2 ላይ ትገኛለች፡፡ ከእነዚህ ጥረቶች መካከል ለሕገ-ወጥ ዝውውር ተጋላጭ የሆኑ ከ10,000 በላይ የሚሆኑ ሰዎችን ሕገ ወጥ ዝውውር መቋረጡ እና ቁጥራቸው ከፍ ያለ ሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ለህግ መቅረባቸው ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ከዚህም ሌላ የውጭ አገራት አሰሪና ሠራተኛና አገናኝ ኤጀንሲዎችን በተሻለ ደረጃ በመቆጣጠር ላይ የሚገኝ ከመሆኑም ሌላ በማኅበረሰብ ውይይት ፕሮግራም አማካኝነት ስለ ሕገ-ወጥ ዝውውር እና ከሕገ-ወጥ ዝውውር ጋር ተያያዥ በሆኑ ወንጀሎች ላይ የተሻለ ግንዛቤ እንዲፈጠር እያደረገ ነው፡፡ ይህም ሆኖ መንግሥት በበርካታ ቁልፍ ጉዳዮች ዙሪያ መሰረታዊ መመዘኛዎችን ሊያሟላ አልቻለም፡፡ መንግሥት ለሃገር ውስጥ ሕገ-ወጥ ዝውውር በቂ መፍትሔ ሊሰጥ አልቻለም፤ ይህም ሕጻናትን ለወሲብ ሲባል በሕገ-ወጥ መንገድ ማዘዋወርን ይካተታል፤ እንዲሁም መንግሥት ከተጋላጭ ስደተኞች መካከል የሕገ-ወጥ ዝውውር ሰለባዎችን አስቀድመው ለመለየት ለሚሰሙ ግምባር ቀደም ምላሽ ሰጪዎች የሚሆን ደረጃውን የጠበቀ የአሰራር ደንብ የለውም፡፡ መንግሥት ለወንድ ተጠቂዎች በቂ ከለላ አያደርግም፡፡ እናም ለሦስተኛ ተከታታይ ዓመት የኢትዮጵያ መንግሥት ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩን ተግባራዊ ለማድረግ ገንዘብ መመደቡን ሪፖርት አላደረገም፡፡

ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ የውሳኔ ሃሳቦች፡ -

በወሲብ እና በሃገር ውስጥ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ በአዘዋዋሪዎች ላይ ምርመራ ለማድረግ እና ለሕግ ለማቅረብ የሚደረገውን ጥረት ይበልጥ ማጠናከር፡፡

• ሃገር ውስጥ እና ድንበር ተሻጋሪ የሕገ-ወጥ ዝውውር ተጠቂዎችን አስቀድሞ ለመለየት ደረጃውን የጠበቀ አሰራር ማጎልበት፡፡

• ለወሲብ እና ሃገር ውስጥ ሕገ ወጥ ዝውውርን ለመመርመር እና ለሕግ ለማቅረብ የሚደረገውን ጥረት የህግ አስከባሪዎችንና የፍትህ አካላት ይበልጥ ማጠናከር፡፡

• ሃገር ውስጥ የወሲብ እና ድንበር ዘለል ሕገ-ወጥ ዝውውር ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን አስቀድሞ ለመለየት የሚያስችል ደረጃውን የጠበቀ አሰራር ማጎልበት፡፡

• ብሔራዊ የፌደራል የአፈፃፀም ዘዴዎችን ወጥ በማድረግ ሥራ ላይ ማዋል፤ ለሁሉም ክልሎች ማሰራጨት፡፡

• በጸረ ሕገ ወጥ ዝውውር አዋጅ እና በሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር እና በሕገ ወጥ የዕቃ ዝውውር መካከል ባለው ልዩነት ላይ ለሕግ አስከባሪ እና የፍትሕ አካላት የተሻለ ሥልጠና ማስጠት፡፡

• የሕገ-ወጥ ዝውውር ሰለባ ለሆኑ ወንዶች የጥበቃ አገልግሎት ማስጠት እና የሚቻል ከሆነ ለሁሉም ሰለባዎች የገንዘብ ወይም በዓይነት ድጋፍ ማስጠት፡፡

- የውጭ አገር የአሠሪ እና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎችን የመቆጣጠር፣ አሠሪና ሠራተኛ አታሼዎችን የመመደብ እና ሕገ-ወጥ ቀጣሪዎችን የመመርመር እና ለፍትሕ የማቅረቡን ስራ አጠናክሮ በመቀጠል የውጭ አገር ቅጥር አዋጅን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ፡፡

- ብሔራዊ መታወቂያ እና ፓስፖርት በማስጠት እና በተሻለ ሁኔታ በማጣራት ለሕጻናት በተጭበረበረ ሁኔታ የሚደሉን አካሄድ ማስቀረት፡፡

- በውጭ አገራት ለሚሰሩ ሠራተኞች ከአገር ከመውጣታቸው በፊት በሚሰጥ ስልጠና ወስጥ በመካከለኛው ምሥራቅ እና በሌሎች አገራት ስላለ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስለ ሠራተኞች መብቶች መረጃን ማካተት፡፡ ገጠሪቱ ኢትዮጵያን አካትቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎች ሁሉንም የአገሪቱን ክፍሎች ማዳረሳቸውን ማረጋገጥ።

- ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩን ለመተግበር ገንዘብ መመደብ፡፡

የክስ ሂደት

መንግሥት በጸረ-ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ዙሪያ ሕግ የማስከበሩን ጥረት ቀጥሎበታል፤ ይሁን እንጂ ይበልጥ ትኩረት በማድረግ ላይ ያለው በሃገር ወስጥ የወሲብ ሕገ ወጥ ዝውውር እና የጉልበት ብዝበዛ ለይ ሳይሆን በድንበር ተሻጋሪ ሕገ ወጥ ዝውውር ላይ ነው፡፡ በ2015 የወጣው ጸረ-ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር አዋጅ ቁ. 909/2015 በወሲብ ምክንያት ወይም ለሥራ ሰዎችን በሕገወጥ ማዘዋወር ሕገ ወጥ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ለእነዚህም ሕገ ወጥ ተግባራት በአዋቂነት የዕድሜደረጃ ላይ ለደረሱ ወንድ ተጠቂዎች ከ15 እስከ 25 ዓመታት የእስር እና ከ150,000 እስከ 300,000 የኢትዮጵያ ብር ($5,350 እስከ $10,700) ቅጣት፣ በአዋቂነት የዕድሜደረጃ ላይ ለደረሱ ሴት ተጠቂዎች ከ25 ዓመት እስከ ዕድሜልክ እስራት እና ከ200,000.00 እስከ 500,000.00 የኢትዮጵያ ብር ($7,130 እስከ $17,830)፣ የገንዘብ ቅጣት ደንግጓል፡፡ እነዚህ ቅጣቶች በበቂ ማጠን ጥብቅ የሚባሉ ሲሆኑ፣ ከወሲብ ሕገወጥ ዝውውር አንጻር ለአስገድዶ መድፈር ከተደነገጉት ጋር ተመጣጣኝ ናቸው፡፡ ፈቃድ የተሰጣቸውን የሠራተኛና አሠሪ አገናኝ ኤጀንሲዎችን ሥራ ይገዛ የነበረው የሠራተኞች ልውውጥ አገልግሎት አዋጅ ቁ. 923/2016፣ አንድ የቅጥር ኤጀንሲ የአዋጁን ድንጋጌዎች በሚጥስ ጊዜ የሚጣሉበትን ልዩ ልዩ ቅጣቶች የያዘ ሲሆን፣ የተጭበረበረ ማስረጃን ወይም ሰነዶችን ማቅረብ ወይም ሠራተኞችን ለመቅጠር ሀሰተኛ ማስታወቂያ ማውጣት የወንጀል ኃላፊነትን እንደሚያስከትል ይደነግጋል፤ ሆኖም ግን የትኛው የወንጀለኛ መቅጫሕግ ክፍል ተፈጻሚነት እንዳለው ለይቶ አልወሰነም፡፡

በ2018 ዓ.ም የፌዴራል እና የክልል የፍትሕ አካላት በ2015 በወጣው ጸረ-ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሕግ ላይ በመመስረት 535 ጉዳዮችን በማየት ላይ ሲሆኑ፣ 1,028 ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች ጥፋተኞች ተብለዋል፤ ከእነርሱ መካከል 240 ያህሉ የእስር ቅጣት ተጥሎባቸዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ ሕገወጥ የዕቃ ዝውውርን ያካተቱ ነበሩ፤ ከሕገወጥ ዝውውር ጋር ሌሎችም ወንጀሎች ተፈጽመዋል፡፡ በ2017፣ መንግሥት በ182 ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች ላይ የጥፋተኝነት ወሳኔ አስተላልፏል። ሆኖም በአገሪቱ ወስጥ ኢትዮጵያዊያን ዜጎችን በበዘበዙ ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች ላይ በህግ ማስከበር ጥረቶች ስለተወሰዱ እርምጃዎች የተገለጸ ነገር የለም፡፡ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ ተሳትፎ በነበራቸው ባለሥልጣናት ላይ ስለተካሄዱ ምርመራዎች፣ ስለቀረቡባቸው ክሶች ወይም የጥፋተኝነት ወሳኔዎች መንግስት ያወጣው ሪፖርት የለም፡፡ የፋይናንስ እና የአቅም ወስንነቶች በክልል ፖሊሶች መረጃ ለማሰብሰብ በሚደረገው ጥረት ላይ እክል ከመፍጠራቸው ሌላ፣ በክልሎች እና በፌዴራል መንግሥት መካከል ያሉ ዝቅተኛ የሥራ ግንኙነት እና አነስተኛ ትብብር ወጤታማ የሕግ ማስከበር ሥራዎች እንዲከናወኑ

አድርገዋል፡፡ መንግሥት በውጭረጂዎች የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸውን ይበልጡን በ2015 ጸረ ሕገ-ወጥ ዝውውር ሥልጠናዎች ለፌደራል እና ለክልል መንግስት ሠራተኞች ለማስጠት ከዓለምዓቀፍ ረጂዎች ጋር ያለውን አጋርነት ቀጥሎብታል።

## ህጋዊ ከለላ

መንግሥት ለሕገ ወጥ ዝውውር ሰለባዎች ጥበቃ ለማድረግ ማስተኛ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል፡፡ መንግስቱ ሰለባዎቹን ለማየት እና ለእነርሱምአገልግሎቶችን ለማስጠት ከዓለምዓቀፍ ድርጅቶች እና ከሚዶች ጋር የቀረበ የሥራ ግንኙነት ማስርቷል፡፡ እንዲህ ላሉት አካላት ገንዘብ ባይመድብምእንኳን፣ እንደ ሜሬት፣ ተቋማት፣ ሠራተኞች እና ሌሎች የሎጂስቲክስ ድጋፎችን እንደ አስፈላጊነቱ መድቧል፡፡ በ2018፣ የፌደራል እና የክልል መንግሥታት በማውኢትዮጵያ ከ10,100 በላይ አዋቂዎች እና ሕጻናትን በሕገወጥ ዝውውር ሂደት ላይ ሳሉ በቁጥጥር ስር ወለዋል፡፡ አብዛኛዎቹ ወደ ባህረ ሰላጤእና አፍሪካ አገራት ለሥራ በሕገወጥ መንገድ በመጓዝ ላይ የነበሩ ናቸው፤ ይህ ቁጥር ባለፈውዓመት ከነበረው10,600 ሰዎች ጋር ተቀራራቢ ሲሆን፣ መንግሥት ከእነዚህ ሰለባዎች መካከል ለጊዜውቁጥራቸውላልታወቀ ሰዎች ማጠለያ፣ ሕክምና፣ የሥነ ልቦና ድጋፍ እና አማራጭየሥራ ዕድሎች ለማግኘት የሚያስችሏቸውን ክህሎቶች እንዲያገኙ ድጋፍ አድርጎላቸዋል፡፡ ነገር ግን ሪፖርት በቀረበበት ዓመት መንግሥት የአገር ውስጥ እና ድንበር ዘለል ሕገ ወጥ ዝውውሮችን አስቀድሞ ለማየት እና አቅጣጫለማስያዝ የሚያስችል ወጥ የአሠራር ሂደት የለውም፡፡ በመሆኑምከእነዚህ ሰለባዎች መካከል የተወሰኑት ተገቢ እንክብካቤ ያላገኙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ መንግሥት ከአንድ ዓለምዓቀፍ ድርጅት ጋር በመሆን በአፋር እና በመተማሁለት ከቦታ ቦታ ዝውውር ተመላሾች ማረፊያ ማዕከላት አደራጅቷል፤ እነዚህ ማዕከላት የመንግሥት ተቋማትን ያለምንምኪራይ እንዲጠቀሙፈቅዷል፡፡ መንግሥት በአዲስ አበባ እና በበርካታ ዋና ዋና ከተማዎች የሕጻናት ጥበቃ ማዕከላትን ሥራ አስቀጥሏል፤ ዓላማውምከገጠር ወደ ከተሞች በሕገወጥ በማዛዋወር ላይ ናቸውየተባሉ ሕጻናትን ለይቶ ማስቆምእና እንክብካቤ ማስጠት ነው፡፡ ፖሊስ እና የሲቪል አገልግሎት ትራንስፖርት ሠራተኞች (በሕገወጥ ዝውውር ላይ ያሉ ሕጻናትን ማየት የሚያስችል ሥልጠና ያገኙ ናቸው) አብዛኛዎቹን በዚህ ሜሉኩየተገኙ ሕጻናትን ወደ ማጠለያዎች እንዲገቡ አድርገዋል፡፡ እንደአመችነቱ የመንግሥት ባለሥልጣን አካላት የማጠለያ፣ የምግብ፣ የትምህርት፣ የጤና እንክብካቤ እና የቤተሰብ ሜልሶ ማዋሃድ አገልግሎቶች ይሰጣሉ፡፡ አንድ በድንበር ዘለል የሕገወጥ ዝውውር ድርጊቶች ላይ በትኩረት የሚሰራ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ለሴቶች እና ለልጆች አጠቃላይ ወደ ቤተሰቦቻቸውየመመለስ አገልግሎቶች፣ ከቤተሰብ ጋር ዳግምየመቀላቀል፣ የጤና እንክብካቤ፣ የአዕምሮ ጤና ምክር፣ ሕገ-ነክ ምክር፣ የምግብእና የማጠለያ እንዲሁምትምህርታዊ ድጋፍ ማስጠቱን ቀጥሎብታል፡፡ ለወንዶች የሕገወጥ ዝውውር ሰለባዎች የሚደረገውድጋፍ አሁንምበቂ አይደለም፡፡ ሆኖምበ2018፣ አንድ ሚድ(NGO) ለተጋላጭወንዶች እና ከቤተሰብ ለተለዩ ሕጻናት ድጋፍ የሚያደርጉ ሁለት ሜልሶ ማቋቋሚያ ማዕከላትን ከፍቷል፡፡ በዓመቱ ወስጥ፣ መንግሥት ከ2,600 በላይ የሆኑ ኢትዮጵያዊያንን ከሳውዲ ዓረቢያ ወደ አገራቸውለማምጣት እና እገዛ ለማስጠት ከአንድ ዓለምዓቀፍ ድርጅት ጋር በትብብር ሰርቷል፡፡ በእርግጥ ይህ ቁጥር በጠቅላላውበዚህች የመካከለኛው ምሥራቅ አገር ከሚገኙ ዜጎች ብዛት አንጻር እጅግ ጥቂት ነው፡፡ መንግሥት ሁሉንምዜጎቹን ከሳውዲ ዓረቢያ ለመመለስ የሚያስፈልገውገንዘብ ስለሌለውበሚመለከታቸውአገራት ሰለባዎችን በማየት አገልግሎቶች ላይ እገዛ አድርጓል፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞለተመላሾች የአየር ቲኬት ዋጋ ቅናሽ እንዲደረግ ድርድር አካሂዷል፡፡ በባህረ ሠላጤአገራት አንዳንድ የዲፕሎማሲ ሚሲዮኖች በየሚሲዮን ቅጥር ግቢ ወስጥ ማጠለያዎች ነበሯቸው፤ በዚያምለተወሰነ ጊዜ የመቆየት ዕድል ነበራቸው፡፡ ሚሲዮኑምሰለባዎቹን በመወከል ከየመንግሥት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶች ጋር አብሮ ሰርቷል፡፡

በ2015 የወጣው የጸረ ሕገ ወጥ ዝውውር አዋጅ ለተጎጂዎች ጥበቃ እንዲሁም መልሶ ለማቋቋም ለሚደረጉ ጥረቶች ለሰለባዎች ድጋፍ ለማድረግ የሚውል የገንዘብ ምንጭ መስርቷል፡፡ የዚህም የገንዘብ ምንጭ በሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ላይ የተጣለ የገንዘብ ቅጣት እና ንብረታቸውን ከመሸጥ የሚገኝ ገቢ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የውጭ ረጂዎች እና ሌሎች የመንግሥት ተቋማት የሚሰጧቸው ድጋፎች ይህንን የገንዘብ ምንጭ ያግዛሉ፡፡ ሆኖም ግን ካለፈው ዓመት ጋር በተመሳሰለ መልኩ፣ መንግሥት ገንዘብ ለመመደብ ስላደረገው ጥረት እና በዚህ መልኩ የተመደበውን ገንዘብ ስለማስተዳደርደር ያቀረበው ሪፖርት የለም፡፡ ብሔራዊ የሪፈራል መርሃ ግብር አሁንም ተግባራዊ አልሆነም፤ ማጠናቀቁም ይፋ አልተደረገም፤ የሕገ ወጥ ዝውውር ሰለባ የሆኑ ሰዎችን ወደ አገልግሎቶች ማስጫዎች የማምራት ስራን የሚያስተባብረው የጸረ-ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ግብረ ኃይል እንዲሆን አድርጓል፡፡ የአለም አቀፍ ድርጅት እና ሌሎች የመንግስት አካላት አቅጣጫ የማስያዝ ሂደትን በማከናወን ጉልህ ድርሻዎችን ተጫውተዋል፡፡ ይህ ዘዴ ለሕገ ወጥ ዝውውር ሰለባዎች ልዩ የማለያ እና የማምረጫ ስልቶችን ይዟል፤ በተጨማሪም በቦሌ ዓለም ዓቀፍ አየር ማረፊያ በፈቃደኝነት ወደ አገራቸው ከሚመለሱ እና በውጭ አገር መንግሥት ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ከሚደረጉ ሰዎች መካከል የሕገ ወጥ ዝውውር ሰለባ የሆኑትን መለየት የዚህ ጥረት አካል ነው፡፡ ሪፖርት በቀረበበት ወቅት፣ የጸረ-ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር የድርጊት መርሃ ግብር ከአንድ ዓለም ዓቀፍ ድርጅት ጋር በመተባበር የሕገ ወጥ ዝውውር ሰለባዎችን በትክክል ለመለየት የሚያግዝ ልዩ የመለያ ቅጽ አዳብሮ ለቁልፍ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች አሰራጭቷል፡፡ ዋነኛው የሰለባዎች አቅጣጫ የማስያዝ ዘዴ ከ2016 ጀምሮ በይፋም ባይሆን ተግባራዊ ሆኖ የቆየ ቢሆንም፡ የሲቪል ማኅበራት ገና በእንጭጭ እንዳለ እና እንዳልተተገበረ ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከውጭ አገር የሚጡ ሰለባዎችን ወደ ማኅበራዊ አገልግሎቶች የማምራት ሥራ በተቋማት መካከል ባለ ዝቅተኛ ቅንጅት እና በኃብቶች ወይም ግብዓቶች እጥረት ምክንያት አሁንም ውስን ነው፡፡ ሆኖም ግን ሪፖርት በቀረበበት ዓመት፣ መንግሥት ሰለባዎችን ለመለየት እና አቅጣጫ የማስያዝ ወጥ የአሰራር ሂደት አጎልብቷል፡፡ ከብሔራዊ የሪፈራል መርሃ ግብር በተጨማሪ፣ የክልል መንግሥታት ከክልል እና ከፌደራል ፖሊስ ጋር አብረው በመሥራት የሕገ ወጥ ዝውውር ሰለባዎችን ወደ መጠለያዎች እና ሌሎች የጥበቃ አገልግሎቶች ይልካሉ፡፡ ይህም ሆኖ መንግሥት አሁንም ቢሆን ከተጋላጮች መካከል የሕገ ወጥ ዝውውር ተጠቂዎችን ለመለየት የሚያስችል ወጥ አሰራር የለውም፤ ይህ በተለይ ለሥራ ወደ ውጭ አገር በሕገ ወጥ መንገድ በሚሄዱ እና ከውጭ አገራት ተመላሽ የሆኑትን ወደ ጥበቃ አገልግሎቶች መላክን (ሪፈር ማድረግን) ይመለከታል፡፡

ባለሥልጣናት ሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎችን በመመርመር እና ለሕግ በማቅረብ ዙሪያ እንደሚያበረታቱ ሪፖርት ቢደረግም፡ በእነዚህ ሂደቶች ወስጥ ንቁ ሚና የነበራቸው ሰለባዎች ቁጥር አይታወቅም፤ እንዲሁም ይህን እንዲያደርጉ ለማስቻል መንግሥት የሕግ ወይም ሌላ ዓይነት ድጋፍ ሰጥቷቸው የነበረ መሆኑ ግልጽ አይደለም፡፡ ከአንድ ዓለም ዓቀፍ ድርጅት በተገኘ የቴክኒክ ድጋፍ፣ መንግሥት በዋና ዓቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ወስጥ ልዩ የምሥክሮች ጥበቃ ክፍል መስርቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ መንግሥት እና በክልል አቻዎቻቸው መካከል ያለውን ትብብር እና አጋርነት ለማጠናከር የሁለት ቀናት የምሥክሮች ጥበቃ ስብሰባ ተካሂዷል፡፡ እንደ አንዳንድ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ኃላፊዎች ከሆነ ልጆች በቪድዮ አማካኝነት በሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ላይ ምሥክርነት መስጠት ችለዋል፡፡ የጸረ-ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ሕግ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ሰለባዎች በኢትዮጵያ ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ እንዲያገኙ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ወደ አገራቸው ለመመለስ እገዛ ስለማድረግ ይደነግጋል፡፡ መንግሥት ሪፖርት በሰጠበት ጊዜ ወስጥ ማንኛቸውም ሰለባዎች ወደ አገር የመመለስ መፍትሔ ያገኙ ስለመሆኑ የገለጸው ነገር የለም፡፡ በ2015 የወጣው የጸረ-ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር አዋጅ በምሥክር እና በመረጃ ሰጪ ጥበቃ አዋጅ (ቁ. 699/2010) ስር የተደነገጉ ጥበቃዎች ለሕገ ወጥ ዝውውር ሰለባዎችም ተፈጻሚ እንዲሆን አድርጓል፤ በዚህም ጥበቃ ስር የሕገ ወጥ ዝውውር ሰለባ በመሆን ምክንያት ለተፈጸሙ ወንጀሎች ከሕግ ተጠያቂነት ማጠበቅን አካቷል፡፡ በ2018 ወስጥ ማናቸውም ሰለባ ተገቢው ማጣሪያ

ሳይደረግ ወዲያውኑ ከአገር እንዲወጣ ስለመደረጉ ወይም ስለመታሰሩ፣ በገንዘብ ስለመቀጣቱ፣ የእስር ቅጣት የተጣለበት ስለመሆኑ፣ ወይም ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች እንዲፈጽሙ ባስገደዷቸው ጥፋቶች ምክንያት የተቀጡ ስለመሆኑ የቀረበ ሪፖርት የለም፡፡ ሆኖም መንግሥት በሕገወጥ ዝውውር ጉዳይ የየበኩላቸውን ምሥክርነት ለማስጠት በሚጠባበቁበት ወቅት ጥቂት ሰለባዎችን በፖሊስ ጣቢዎች እንዲቆዩ አድርጓል፡፡ በመደበኛ የማለየት እና አቅጣጫ የማስያዝ ሥርዓት፣ አንዳንድ የሕገወጥ ዝውውር ሰለባዎች በሕግ ማስከበር ሥርዓቱ ወስጥ ተለይተው ሳይታወቁ ቀርተው ሊሆን ይችላል፡፡

## የመካላከል ስራዎች

መንግሥት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመካላከል የሚያደርገውን ጥረት ጨምሯል፡፡ በዓመቱ ወስጥ የጸረ-ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ግብረ ኃይል በየስድስት ወሩ ስብሰባ አድርጎ አዲስ ጸሐፊ መርጧል፤ ጸሐፊውም በመጣናኛ ብዙሃን ቀርበው ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በኢትዮጵያ ከፍተኛ ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይህ ግብረ ኃይል በሦስት ንዑሳን ቡድኖች ተከፍሏል፡- መካላከል፣ ከለላ ማስጠት እና ክስ፡፡ ሆኖም ግን ፓርላማው በ2016 ያጸደቀውእና ልዩ ልዩ ሕገወጥ ዝውውርን ለመካላከል የሚያስችሉ ተግባራትን ያካተተው ብሔራዊ የሰብዓዊ መብቶች የድርጊት መርሃ ግብር 2016-2020 የመገናኛ ብዙሃን ዘመቻን እና በከተሞች ማዕከላት የሴቶች እና የሕጻናት ሰለባዎችን ለማገዝ የሚደረጉትን ጥረቶች ጨምሯል፡፡ ሆኖም ግን ዕቅዱ ለሦስተኛ ተከታታይ ዓመት ለዚህ ትልም ተግባራዊነት የመደበው ገንዘብ የለም፡፡ የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ማሥሪያ ቤት ከአንድ ዓለም ዓቀፍ ድርጅት እና የትምህርት ተቋም ጋር በመጣመር፣ ስለሕገወጥ ዝውውር የሚያወሳ መመሪያ ለሕዝብ ማሰራጨቱን፣ በልዩ ልዩ የአማራ ወረዳዎች ወስጥ የጸረ-ሕገወጥ ሰዎችን ዝውውር ፊልም ማሳየቱን ቀጥሎበታል፤ እንዲሁም ለግብረ ኃይል አባላት በሕዝብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ላይ የምርጥ ተሞክሮዎች ሥልጠና ሰጥቷል፡፡ የአካባቢ እና የክልል አስተዳደሮች፣ ከአንድ ዓለም ዓቀፍ ድርጅት ጋር በመተባበር፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ "የማኅበረሰብ ወይይት" መድረኮችን ማዘጋጀታቸውን ቀጥለውበታል፡፡ የእነዚህ መድረኮች ዓላማ በመላው አገሪቱ በታችኛው የሕብረተሰብ ክፍል ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ ከአገር መውጣት የሚያስከትላቸውን ስጋቶች በተመለከተ ግንዛቤ ማሳደግን ዒላማ ያደረገ ነው፡፡ በዚህ ጥረት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ መድረስ ተችሏል፡፡ በእነዚህ ወይይቶች አማካኝነት ማኅበረሰቦች የተጠረጠሩ ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎችን እና ደላሎችን በማጠቆም ረገድ በንቃት እንዲሳተፉ አበረታተዋቸዋል፡፡ በእነዚህ መድረኮች በማጠቀም መንግሥት ወደ ባህረሠላጤ አገራት የሚደረጉ ጉዞዎችን በተመለከተ መንግሥት ሕጋዊ ማሥመር ለማስያዝ የወሰዳቸውን እርምጃዎች ለሕዝቡ ለማስተዋወቅ ተችሏል፡፡ በመንግሥት ትብብር እና በዓይነት በተደረገ ድጋፍ አማካኝነት አንድ ዓለም ዓቀፍ ድርጅት በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይ እና በሌሎች ክልላዊ መንግሥታት ለወይይት አመቻቾች ሥልጠና ሰጥቷል፤ ከዚህም ሌላ ሕግ አስከባሪ አካላት ስለሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች እና ከዚያም በላይ ስለሕገወጥ አዘዋዋሪዎች ኔትወርክ ጥቆማ ሊሰጥ ስለሚችልበት ሁኔታ 1,890 የማኅበረሰብ የወይይት ቡድኖች አቋቁሟል፡፡ ከዚህም ጥረት በማሳት ሪፖርት በተደረገበት ወቅት ወስጥ በወል ያልታወቁ ቁጥር ያላቸው የምርመራ ሥራዎችን ማስራት ጀምረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመላው አገሪቱ ያሉ ባለሥልጣናት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ስለሚያስከትላቸው አደጋዎች በህብረተሰቡ ዘንድ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ በቴሌቪዥን እና በሬዲዮ ማስታወቂያዎች ተነግረዋል፣ ቃለ ማጠይቆችም ተካሂደዋል፡፡ በዚህ አነሳሽነት ሰፊው ሕዝብ፣ የኃይማኖት እና ባሕላዊ መሪዎች፣ ሽማግሌዎች እንዲሁም የሚዲያ ሠራተኞች ዘንድ ለመድረስ ተችሏል። ይህም ሆኖ ከላይ የተገለጸው ግንዛቤ የመፍጠር ዘመቻ ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ወደ ሌሎች አገራት መሄድ እና ሰዎችን በሕገወጥ መንገድ ማዘዋወር የሚያስከትላቸው አደጋዎች በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች ባለማስረፃቸው በቂ ግንዛቤ የተገኘበት ነው ለማለት አይቻልም፡፡

በ2016 ቢሻሻልም እንኳን፣ ይህ ሪፖርት በቀረበበት ዓመት መንግሥት አሠሪና ሠራተኛ አዋጁን ተግባራዊ አላደረገም፡፡ የተሻሻለው የውጭ አገራት ቅጥር አዋጅ በግል የቅጥር ኤጀንሲዎች ላይ ይበልጥ ቁጥጥር እንዲደረግ፣ በውጭ አገራት ያሉ የሕገወጥ የሰው ዝውውር ሰለባ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ሠራተኞችን እንዲያግዙ በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች የአሰሪና ሠራተኛ አታሼዎች እንዲመደቡ እንዲሁም ወደ ውጭ አገር ሄደው የሚሰሩ ሠራተኞችን የሚለይ እና የሚያሰለጥን ገለልተኛ ኤጀንሲ እንዲቋቋም ይደነግጋል፡፡ ሁለት ተጨማሪ የአዋጁ ክፍሎች አዋጁን በሚጥሱ የቅጥር ኤጀንሲዎች ላይ ስለሚጣለው ቅጣት እና በውጭ አገር ሠራተኛ እና አሰሪ አገናኝነት ለመሥራት ፈቃድ ስለሚሰጥበት እና ማስታወቂያ ስለሚነገርበት ሁኔታ (ለምሳሌ በሃሰተኛ ማስታወቂያ፣ ፓስፖርትን ስለመቀማት እና ስለመብቶች ጥሰት) ደንቦች አስቀምጠዋል፡፡ በተሻሻለው አዋጅ፣ የውጭ አገር ሠራተኛና አሰሪ ኤጀንሲዎች በዋስትናነት የሚቀመጥ እና የሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ የሆኑ ሰዎችን ወደ አገራቸው መመለሻ የሚውል ብር አንድ ሚሊዮን ($35,660) በባንክ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡ ሪፖርት በቀረበበት ወቅት መንግሥት እነዚህን ጥብቅ የሚመለከቻ ማስፈርቶች ካስቀማጠበኋላ 135 የግል የቅጥር ኤጀንሲዎች ማስፈርቶቹን በማሟላት ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ናቸው ብሎ ወስኗል፡፡ በ2018 መንግሥት 616 የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ መርማሪዎች በማሰማራት በግምት 38,000 ያህል የሠራተኞች ሁኔታዎችን መደበኛ የሥራ ቦታዎች መርመረዋል፡፡ ሆኖም ግን በእነዚህ ምርመራዎች ምክንያት ስለታገዱ ፈቃዶች ወይም በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ላይ ስለተፈጸሙ ጥሰቶች ብዛት ሪፖርት አልተደረገም፡፡ ለዚህም እንደ አንድ ምክንያት የሚወሰደው ስለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ያለ ዝቅተኛ ግንዛቤ ነው፡፡ መንግሥት ለሥራ ሁኔታዎች መርማሪ 5.8 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ($206,850) በመመደብ ሙሉ የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል፡፡ ሪፖርት በቀረበበት ዓመት ከሳውዲ ዓረቢያ ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት ሲፈርም፣ ከዩናይትድ አረብ ኤሚሬትስ፣ ከኩዌት እና ኦማን ጋር ተመሳሳይ የቅጥር ስምምነቶች ለመፈረም ድርድር ማድረጉን ቀጥሏል፡፡ ኢትዮጵያ ከኳታር እና ከጆርዳን ጋር እነዚህን መሰል ስምምነቶች ነበሯት። በእነዚህ ስምምነቶች ፈራሚዎች ኢትዮጵያዊያን ሠራተኞችን በተመለከተ ሥነ ምግባርን የጠበቀ ቅጥር እንዲፈጽሙ፣ ሕጉን በሚጥሱ ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስዱ እና በሕግ ፊት እኩል ጥበቃ የማግኘት መብትን እንዲያስከብሩ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንዲሁም ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ እንዲከፍሉ፣ ምክንያታዊ የሥራ ሰዓታት እና የእረፍት ጊዜ እንዲካተቱ ስምምነቱ ይጠይቃል፡፡ በሪፖርቱ ዓመት በተለይ በዓረብ አገራት ሥራ ለሚፈልጉ ሠራተኞች ከጉዞ በፊት ሥልጠና ማስጠት እና ስለመብቶቻቸው እና በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ምክንያት ሊያጋጥማቸው ስለሚችሉ አደገኛ ሁኔታዎች የማሳወቅ ሥራ ተጀምሯል፡፡ የኢትዮጵያ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶች በ2012 በወጣው ህግ መሠረት በመላ አገሪቱ ሁሉም ልደቶች እንዲመዘገቡ በመደረግ ላይ ናቸው፡፡ ነገር ግን በመላ አገሪቱ ወጥነት ያለው መታወቂያ አለመኖሩ ይህንን ሕግ ለመፈጸም የሚደረገውን ጥረት በሚደናቀፍ ላይ ይገኛል፡፡ አሁንም በወረዳ ደረጃ የሚሰጡ መታወቂያዎች በማስጠት ላይ ሲሆኑ፣ ይህም ለማጭበርበር የተጋለጠ ነው፡፡ በሪፖርቱ ዓመት መንግሥት ለወሲብ ንግድ እና ለጉልበት ብዝበዛ ያለን ፍላጎት ለመቀነስ ጥረት መደረጉን ገልጾዋል፡፡ አንድ የውጭ አገር ረጂ እና አሜቻች ኢትዮጵያዊያን ወታደሮች ለዓለም ዓቀፍ የሰላም ማስከበር ሚሲዮኖች ከማሰማራታቸው በፊት የጸረ-ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ስልጠና እንዲያገኙ አድርጓል፡፡

የሕገወጥ ሰዎች ዝውውር ገፅታ

ባለፉት አምስት ዓመታት ሪፖርት እንደተደረገው፣ ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች በኢትዮጵያ በአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ሰለባዎችን ይበዘብዛሉ፡፡ እንዲሁም ሕወገጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን ይበዘብዛሉ፡፡ የኢኮኖሚ ዕድሎች ጥቂት መሆናቸው፣ በአገሪቱ ያለ ከፍተኛ ድህነት እና ቤተሰብም ስለሚያበረታታ በሺዎች የሚቆጠሩ ያላገቡ፣ ዕድሜያቸው ከ30 በታች የሆነ ኢትዮጵያዊያን በዋናነት በጅቡቲ ወይም ሶማሊያ በኩል ወደ የመን፣ ከዚያ ወደ ሳውዲ ዓረቢያ እንዲሁም ወደ አውሮፓ ይሻጋገራሉ፡፡

በሕገወጥ መንገድ ድንበር አቋርጦ ወደ ኬኒያ መግባት ተለምዷል፤ የሕገወጥ ዝውውር ሰለባዎች ወደ ደቡብ አፍሪካ በመግባት ከዚያ ወደ ኤኳዶር በረውበሜጨረሻም ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ወይምካናዳ ለመግባት አልመው ይጓዛሉ፡፡ ብዙምየሚዘወተረውመንገድ በሱዳን እና ሊቢያ በኩል አድርጎ ወደ ሜዲትራኒያን፣ በሜጨረሻም አወሮፓ መግባት ነው፡፡ ከላይ ከተገለጹት ሦስት መንገዶች በገዛ ፈቃዳቸውኢመደበኛ ጉዞ የሚጀምሩ ኢትዮጵያዊያን የኋላ ኋላ በሚያልፉባቸውአገራትም ሆነ በመዳረሻውአገር ለወሲብ ብዝበዛ ወይምለግዱታ ሥራ እንደሚጋለጡሪፖርቶች ያመላክታሉ፡፡ አንድ ዓለምዓቀፍ ድርጅት ባወጣውሪፖርት ሳወዲ ዓረቢያ ለመግባት በማሰብ በምሥራቅ አቅጣጫወደ የመን የሚጓዙ ዕድሜያቸውያልደረሰ ሕጻናት ቁጥር ጨምሯል ብሏል፡፡ በዓመት በግምት 100,000 የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን ለሥራ በሕገወጥ መንገድ ወደ ሳወዲ ዓረቢያ ይጓዛሉ፤ ይህ ጉዞ አደገኛ ነው፤ ምክንያቱምየባሕር ጉዞ፣ የእርስ በእርስ ጦርነት ስላለ እና በየመን በአጠቃላይ ሥርዓት አልበኝነት የነገሠ በመሆኑ ነው፡፡ በተለይ ባለፉት ዓመታት፣ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች በሱዳን በኩል አድርገውወደ አወሮፓ ለመጓዝ ይሰደዳሉ፡፡ ወጣት ሴቶች ደግሞየቤት ወስጥ ሠራተኛ ለመሆን በማሰብ በኤርትራ እና በጅቡቲ በኩል ወደ ሳወዲ ዓረቢያ ይጓዛሉ፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት በኦክቶበር ወር 2013 ሴቶች በባህረሠላጤአገራት የቤት ወስጥ ሥራ ለማግኘት በሚፈጽሙት ቅጥር ላይ እገዳ ጥሎየነበረ ሲሆን፣ በሴፕቴምበር 2018 የሁለትዮሽ ስምምነት ወደተደረገባቸውአገራት ማለትም ወደ ኳታር፣ ሳወዲ አረቢያ እና ጆርዳን የሚደረጉ ጉዞዎች ላይ የተጣለውን ዕገዳ አንስቷል፡፡ እገዳውበኢመደበኛ መንገድ ከአገር ለመውጣት እና ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር የራሱን አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡ ሳወዲ ዓረቢያ አሁንምዋነኛ የኢመደበኛ ጉዞዎች መዳረሻ ስትሆን፣ ከ80-90 በመቶ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን ሥራ ለማግኘት በሕገ ወጥ መንገድ የሚጓዙት ወደዚያውነው፤ ከ200,000 በላይ ኢትዮጵያዊያን በሳወዲ ዓረቢያ እንደሚኖሩ ሪፖርት ተደርጓል፡፡ ከማርች እስከ ኖቬምበር 2017፣ ሁሉምበሕገወጥ መንገድ ወደ ሳወዲ ዓረቢያ የገቡ ሁሉምየውጭአገር ዜጎች በፈቃዳቸውአገሪቱን ለቅቀውእንዲወጡየጊዜ ገደብ አስቀማጡች፡፡ አንድ ዓለምዓቀፍ ድርጅት ሪፖርት እንዳደረገውበዚህ ጊዜ ወስጥ ከ100,000 በላይ ኢትዮጵያዊያን ወደ አገራቸውተመልሰዋል፡፡ ከእነርሱ መካከል 65,000 ያህሉ በመንግሥት እንዲወጡየተደረጉ ሲሆኑ፣ 70 በመቶውወንዶች ናቸው፡፡ አንደ አንድ ሚያድ(NGO)፣ ለቤት ወስጥ ሥራ ወደ መካከለኛውምሥራቅ አገራት የሚጓዙ ሴቶች እና ልጃገረዶች ቁጥር እያሻቀበ ነው፡፡ በመካከለኛውምሥራቅ በሥራ ላይ የሚሰሙ በርካታ ሴቶች አስከፊ ጥቃቶች ያጋጥሟቸዋል፤ ማለትምአካላዊ እና ወሲባዊ ጥቃት፣ ደመወዝ መከልከል፣ እንቅልፍ መንሳት፣ ፓስፖርት መቀማት እና እገታ ይደርስባቸዋል፡፡ ለስራ ከአገር የሚወጡወይምበመካከለኛውምሥራቅ ጥቃት የሚያደርሱባቸውን አሰሪዎች የሚሸሹ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች ለወሲብ ሕገወጥ ዝውውርምየተጋለጡናቸው፡፡ ኢትዮጵያዊያን አዋቂ እና ወጣት ወንዶች ወደ ዓረብአገራት እና ሌሎች የአፍሪካ አገራት በመጓዝ ለጉልበት ብዝበዛ ይጋለጣሉ፡፡

በአገር ወስጥ በተለይ ወደ ትልልቅ ከተሞች የቤት ስራ ለማግኘት በማሰብ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር የሚፈፀም ሲሆን የችግሩን ትክክለኛ ማጠን መገመት ያዳግታል፡፡ የአገር ወስጥ ሚያዶች(NGOs) የአገር ወስጥ ሕገወጥ ዝውውር ሰለባዎች ከውጭአገር ሕገወጥ ሰውዝውውር ሰለባዎች በቁጥር እንደሚበልጡይገልጻሉ፤ በተለይ ደግሞ ሴቶች በወሲብንግድ እና በቤት ወስጥ ሠራተኝነት ብዝበዛ ይደርስባቸዋል፡፡ በ2016 የሜጨረሻ ወራት ረዘም ያለ ጊዜ የፈጀ ግጭት ስለነበረ፣ ወደ ጅቡቲ በመግባት ጥገኝነት የሚጠይቁ የኦሮሞተወላጆች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መምጣቱን አገሪቱ ገልጻለች፡፡ ቀደምት ሰነዶች እንደሚያሳዩት የትግራይ ተወላጆች በአማራ ክልል ያጋእመውን በብሔር ላይ የተመሠረተ አለመረጋጋት በመሸሽ ከአማራ ክልል ወደ ትግራይ ገብተዋል፡፡ ሪፖርት በቀረበበት ወቅት በአገር ወስጥ ግጭት እና በድርቅ ምክንያት በአገር ወስጥ የተፈናቀሉ እና በዚህም ምክንያት ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጋላጭየሆኑ ዜጎች ወደ ሦስት ሚሊዮን በመድረስ ከፍተኛ እመርታ አሳይቷል፡፡ አሁንምቤተሰቦች በኢመደበኛ መንገድ ወደ ወጩአገራት የሚደረጉ ጉዞዎችን በገንዘብ ይደግፋሉ፤

እንዲያውም ልጆቻቸው ወደ ውጪ አገር ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ወደሚገኙ ከተሞች ሄደው ሥራ እንዲፈልጉ ያስገድዷቸዋል ወይም ይገፋፏቸዋል፡፡ አንድ ዓለም ዓቀፍ ድርጅት እንደገመገመው ብዙዎቹ ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች እጅግም አቅም የሌላቸው ሲሆኑ፣ ብዙውን ጊዜ በተጠቂዎች ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ ይህም ሆኖ ይበልጥ የተደራጁ፣ መዋቅራዊ እና ተዋረድነት ያላቸው ሕገወጥ አዘዋዋሪዎችም አሉ፡፡ ሠራተኛ አገናኞች ብዙውን ጊዜ ከሰፊዎቹ ገጠራማ አካባቢዎች ወጣቶችን ዒላማ አድርገው ይንቀሳቀሳሉ፤ በዚህም ወቅት የተሻለ ሕይወት ይኖራችኋል በማለት ለሥራ ፈላጊዎች የሃሰት ቃል ይገባሉ፡፡ ድህነት ከተንሰራፋባት ገጠሪቱ ኢትዮጵያ የመጡ ሴቶች ልጆች በአገሪቱ ውስጥ ለቤት ውስጥ ሥራ እና ለወሲብ ንግድ ይጋለጣሉ፤ ወንዶች ልጆች ደግሞ በሽመና፣ በግንባታ፣ በግብርና እና በመንገድ ላይ ንግድ ለብዝበዛ ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ ወጣት ሴቶች በአዲስ አበባ ማዕከላዊ ገበያ አካባቢ ባሉ በርካታ ሴተኛ አዳሪዎች በሚገኙባቸው ስፍራዎች ለወሲብ ብዝበዛ እንደሚጋለጡ የሚያመላክቱ ሪፖርቶች አሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ቀደም ሲል በጎረቤት የአፍሪካ አገራት በተለይ በጅቡቲ እና በሱዳን በቤት ውስጥ ሠራተኛነት እና በወሲብ ለብዝበዛ ተጋልጠዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን ወንዶች ልጆች አንዳንድ ጊዜያት በጅቡቲ በሱቅ ውስጥ፣ በቤት ውስጥ ሥራ እና በመንገድ ላይ ልመና እንዲሰማሩ ከመደረጉም ሌላ በወንጀል ድርጊትም እንዲሳተፉ ይገደዳሉ።